፲፤ ወኮነኖሙ ለ፳ኤል ፯ተ ዓመተ ወሞተ ሐሴቦን ወተቀብረ ውስተ ቤተልሔም ፤

ሐሴቦንም መስፍን ሆኖ እስራኤልን ሰባት ዓመት ገዝቷቸው ሙቶ በሀገሩ በቤተልሔም ተቀበረ ፤

፲፩፤ ወኮነኖሙ እምድኅሬሁ ለ፳ኤል ኤሎም ዛብሎናዊ ፲ተ ዓመተ፤

ከእሱም በኋላ ከነገደ ዛብሎን የተወለደ ኤሎም ፳ኤልን ፲ ዓመት መስፍን ሆኖ ገዛቸው፤ እንደ ነቢይም ሆኖ አስተማራቸው፤

፲፪፤ ወሞተ ኤሎም ዛብሎናዊ በሴሎም ወቀበርዎ ውስተ ምድረ ዛብሎን ፤

ከዛብሎን ወገን የተወለደ ኤሎምም የተሰጠውን ዘመን ፈጽሞ በሴሎም ሙቶ በዛብሎን ዕጣ ውስጥ ቀበሩት ፤

፲፫፤ ወኮነኖሙ ለ፳ኤል እምድኅሬሁ ሎቦን ወልደ ኤሎም ኤፍራታዊ ፤

ኤሎም ከሞተ በኋላም የኤፍራታው ሰው የኤሎም ልጅ ሎቦን መስፍን ሆኖ እስራኤልን ገዛቸው ፤

፲፬፤ ወተወልዱ ሎቱ ፵ ደቂቅ ወ፴ ደቂቀ ደቂቁ ወይጼዕኑ ላዕለ ሰብዓ አዕዱግ ወኮነኖሙ ለ፳ኤል ፰ ዓመተ ፤

ለሎቦንም ፵ ወንዶች ልጆች ተወለዱለት ፤ የልጅ ልጆቹም ፴ ነበሩ ፤ እነዚህም ፸ው ልጆች በ፸ በቅሎዎች ላይ ይቀመጡ ነበር ፤ እሱም መስፍን ሆኖ ፳ኤልን ፰ ዓመት ገዛቸው እንደ ነቢይም ሆኖ አስተማራቸው ፤

፲፭፤ ወሞተ ሎቦን ወልደ ኤሎም ኤፍራታዊ ወቀበርዎ ውስተ ኤፍራታ ውስተ ኤፍሬም ውስተ ደብረ ረንቅ ፤

የኤፍራታው ሰው የኤሎም ልጅ ሎቦንም በተፈጥሮ የተሰጠውን ዘመን ፈጽሞ በሞተ ጊዜ በኤፍሬም ዕጣ ውስጥ ባለ በሀገሩ በኤፍራታ ከኖራ ግንብ ውስጥ አግብተው ቀበሩት ::

## ምዕራፍ ፲፫
## ጉባኤ

፩፤ ወደገሙ ደቂቀ ፳ኤል ገቢረ እከይ ቅድመ እግዚአብሔር ወአግብአሙ ውስተ እደ ኢሎፍሊ ፵ ዓመተ፤

የ፳ኤልም ልጆች ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረጉ ማለት ኃጢአት ሠሩ፤ ጣዖት አመለኩ ፤ እግዚአብሔርም ፵ ዘመን በኢሎፍላውያን እጅ አሳልፎ ጣላቸው ፤

ነበርና እሥራ አንዱ ነገደ እስራኤል የሸሸን መስለን ከሀገር ወደጐዳና እናርቃቸው አሉ ፤ ለመክበብ እንዲመቻቸው ፤

፴፫፤ ወተንሥኡ ኵሎሙ ዕደወ ፳ኤል እምነ መካኖሙ ወተቃተሉ በበአልታምር ወማዕገቶሙኒ ለ፳ኤል ተበአሱ በመካኖሙ እም ዐረቢሃ ለገባዖን ፤

የእስራኤል ወገኖች ሁሉ ሸሽተው በበአልታምር ከደረሱ በኋላ አግባ መልስ ብለው ይዋጉ ጀመር ፤ ከባቢ /ድብቅ ጦር/ አድርገው ያኖሯቸውም ሰዎች ከገባዖን ምዕራብ ከተሠወሩበት ቦታ ሁነው ያወኩ ይደነፉ ጀመር ፤

፴፬፤ ወገብኡ እንተ ቅድሜሃ ለገባዖን ፲፻ ብእሲ ኅሩያን እም ፳ኤል ወጸንዐ ቀትል ወእሙንቱሰ ኢያአመሩ ከመ በጽሐቶሙ እከዮሙ ፤

ከ፳ኤል የተመረጡ ዕልፍ ሰዎች ወደገባዖን ፊት ለፊት ገቡ ፤ ሰልፉም እየጸና ሄደ፤ የብንያም ወገኖች ግን ፍዳ ኃጢአታቸው እንደደረሰባቸው አላወቁም ነበርና ፤

፴፭፤ ወአውደቆሙ እግዚአብሔር ለብንያሚ ቅድመ ፳ኤል ወቀተልዎሙ ደቂቀ ፳ኤል ለብንያሚ ፪ት ፼ፌ ወ፻ ወ፭ደ፻ተ ወኵሎሙ እለ ይፀውሩ ኵናተ ፤

እግዚአብሔርም የብንያምን ወገኖች በ፳ኤል ፊት ጣላቸው፤ የ፳ኤል ልጆች ነገደ ብንያምን አጠፏቸው ፤ ያን ጊዜ የሞቱት ሃያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ናቸው ፤ የሞቱትም ሁሉ በቀኝ እጃቸው የሚወረውሩ በግራ እጃቸው የሚመክቱ አርበኞች ናቸው፤ /ሐተታ/ ሲወጡ ሁለት እልፍ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ነበሩ፤ ስድስቱ መቶ በኵኵሐሬሞን ገብተው ድነዋል ፤

፴፮፤ ወርእየ ብንያሚ ከመ ተቀትለ ወወሀብዎሙ ፳ኤል መካነ እስመ ተአመኑ በማዕገቶሙ ዘሤሙ ላዕለ ገባዖን ፤

የብንያም ወገኖችም ድል እንደሆኑ አይተው ፳ኤል በገባዖን ባኖሯቸው ከባቢ ጦራቸው ታምነዋልና የሚሸሹበት የወንድ በር ሰጧቸው ፤

፴፯፤ ወሖሩ እልክቱ እለ ዐገቱ ወቀተልዋ ለሀገር በአፈ ሐፂን ፤

ገባዖንን ከበው የተቀመጡትም አርበኞች ከተማ ገብተው አገሩን በእሳት ሰውን በስለት አጠፉ ፤

፴፰፤ ወአዘዝዎሙ ፳ኤል ለእለ የዓግቱ ከመ በሐፂን ይቅትልዎሙ ወያዕርግዎሙ ለጢስ ሀገር ከመ ማኅፈድ ፤

